legal aiddc

መብትዎን ይወቁ

# የሕዝብ ክፍያ ደንብ

## የሕዝብ ሸክምነት (Public Charge) ማለት ምን ማለት ነው?

የቋሚ መኖሪያ ፈቃድ (ግሪን ካርድ) ወይም ወደ አሜሪካ ለመግባት ቪዛ የሚያመለክቱ ሰዎች «የሕዝብ ሸክምነት» (Public Charge) ምርመራን ማለፍ አለባቸው። ይህ ምርመራ ግለሰቡ በአሁኑ ወቅት ወይም ወደፊት በዋነኝነት የመንግሥት እርዳታዎች ላይ ጥገኛ ሊሆን ይችላል ወይ የሚለውን ሁኔታ ይመረምራል፤ ጥገኛ ሊሆን ይችላል ተብሎ ከተገመተ ግለሰቡ እንደ «የሕዝብ ሸክም» ይቆጠራል። የኢሚግሬሽን ባለሥልጣናት የሰውን አጠቃላይ ሁኔታ ይመለከታሉ፤ ይህም ዕድሜን፣ ገቢን፣ ጤናን፣ ትምህርትን ወይም ክህሎትን እና የቤተሰብ ሁኔታን ያካትታል። መንግሥት አመልካቹ «የሕዝብ ሸክም» ሊሆንና በመንግሥት እርዳታዎች ላይ ሊደገፍ ይችላል ብሎ ካመነ፣ የማመልከቻ ጥያቄው ውድቅ ሊያደርግ ይችላል።

## ምን እየተቀየረ ነው?

የፌደራል የአገር ውስጥ ደህንነት መሥሪያ ቤት (DHS) አንድ የቪዛ/ግሪን ካርድ አመልካች «የሕዝብ ሸክም» ሊሆን ይችላል በሚል በሚወስንበት ጊዜ የትኞቹን የመንግሥት እርዳታዎች ማየት እንደሚችል ደንቡን እየቀየረ ነው።

በነበረው አሮጌ ደንብ መሠረት ሁለት ዓይነት የመንግሥት እርዳታዎች ብቻ ነበሩ የሚታዩት፦ እንደ SSI እና TANF ያሉ የገንዘብ ድጋፎች፣ እና በመንግሥት ወጪ የሚደረጉ የረጅም ጊዜ የእንክብካቤ ተቋማት አገልግሎቶች (ለምሳሌ ሜዲኬድ/Medicaid ለአረጋውያን መንከባከቢያ ወይም ለአእምሮ ጤና ተቋማት ወጪ የሚከፍለው)። ከለውጡ በኋላ፣ DHS **ማንኛውንም** በገቢ መጠን ላይ የተመሠረተ («means-tested») የመንግሥት እርዳታ ግምት ውስጥ ማስገባት ይችላል። «በገቢ መጠን ላይ የተመሠረተ» (Means-tested) ማለት ከተወሰነ የገቢ ጣሪያ በታች ያሉ ሰዎች ብቻ የሚያገኙት ጥቅማጥቅም/እርዳታ ነው። ከ SSI እና TANF በተጨማሪ፣ በገቢ መጠን ላይ የተመሠረቱ የመንግሥት እርዳታዎች ሜዲኬድ (Medicaid)፣ አልያንስ (Alliance) እና SNAP (የምግብ ስታምፕ) ያካትታሉ።

በነበረው አሮጌ ደንብ መሠረት፣ DHS ይመለከት የነበረው ግሪን ካርድ የሚያመለክተው ግለሰብ የመንግሥት እርዳታ ማግኘቱን ብቻ ነበር፤ መሥሪያ ቤቱ በቤተሰብ አባላት የተወሰዱ እርዳታዎችን ግምት ውስጥ አያስገባም ነበር። በአዲሱ ደንብ መሠረት፣ DHS የግለሰቡ ቤተሰብ አባላት የመንግሥት እርዳታ ማግኘታቸውን ማየትና ግምት ውስጥ ማስገባት ይችላል። ለምሳሌ፣ አንድ ወላጅ ለግሪን ካርድ ካስመዘገበ፣ DHS ልጃቸው — የአሜሪካ ዜጋ የሆነ ልጅን ጨምሮ — ሜዲኬድ (Medicaid) የሚያገኝ ከሆነ ያንን ግምት ውስጥ ሊያስገባ ይችላል።
DHS እነዚህን ለውጦችና እንዴት ሥራ ላይ እንደሚውሉ የሚያብራራ ተጨማሪ መመሪያ ወደፊት ያወጣል።

| | ከዚህ በፊት | በኋላ |
| --- | --- | --- |
| **<u>የትኞቹ</u> ፕሮግራሞች በግሪን ካርድ ወይም በቪዛ ማመልከቻዬ ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ?** | እንደ SSI እና TANF ያሉ **የገንዘብ** ድጋፎች ብቻ | እንደ SSI እና TANF ያሉ የገንዘብ ድጋፎች፣ **እንዲሁም** በገቢ መጠን ላይ የተመሠረቱ ማናቸውም ፕሮግራሞች Medicaid እና SNAP ጨምሮ |
| **<u>የማን</u> እርዳታዎች በግሪን ካርድ ወይም በቪዛ ማመልከቻዬ ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ??** | **የእርስዎ** ግላዊ ጥቅማጥቅሞች/እርዳታዎች ብቻ | የእርስዎ ግላዊ እርዳታዎች **እንዲሁም** የአሜሪካ ዜጎችን ጨምሮ የቤተሰብዎ እርዳታዎች |

## ለውጡ መቼ ነው ሥራ ላይ የሚውለው?

ለውጡ ሴፕቴምበር 18 ቀን፣ 2026 ዓ.ም ሥራ ላይ ይውላል። ይህ ማለት፦

- ከሴፕቴምበር 18 ቀን፣ 2026 በፊት ለግሪን ካርድ የሚያመለክት ማንኛውም ሰው ላይ ተግባራዊ አይሆንም።
- እስከ ሴፕቴምበር 18 ቀን 2026 ድረስ፣ DHS ማየት ያለበት የገንዘብ እርዳታዎችን (cash assistance) እና በመንግሥት ወጪ የሚደረጉ የረጅም ጊዜ ተቋማዊ እንክብካቤዎችን ብቻ ነው።

## ምን አልተቀየረም?

የሕዝብ ሸክምነት ሕግ በማን ላይ እንደሚሠራ አልተቀየረም። በእነዚህ ወገኖች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፦

- የአሜሪካ ዜጎች፤
- ግሪን ካርድ ያላቸውና የሚያድሱ ወይም የአሜሪካ ዜግነት ለማግኘት የሚያመለክቱ ሰዎች (ነገር ግን ከአገር ውጭ ከስድስት ወር በላይ ከተቀመጡ ሊመለከታቸው ይችላል)፤ እና
- TPS፣ የ U ወይም T ቪዛ፣ የጥገኝነት ጥያቄ (Asylum) ወይም የስደተኛ (Refugee) ደረጃ፣ ወይም የልዩ ኢሚግራንት ታዳጊዎች ሁኔታ (Special Immigrant Juvenile Status) ያላቸው ሰዎች (ነገር ግን በቤተሰብ አማካኝነት ለሚገኝ ግሪን ካርድ ካስመዘገቡ ሊመለከታቸው ይችላል)።

DHS አሁንም ቢሆን በገቢ መጠን ላይ ያልተመሠረቱ የመንግሥት ጥቅማጥቅሞችን ግምት ውስጥ አያስገባም። እነዚህም የሚያካትቱት፦

- የስራ አጥነት ድጎማዎች፤
- ሜዲኬር፤
- ሶሻል ሴኩዩሪቲ ዲሴብሊቲ ኢንሹራንስ (SSDI)፤ እና
- የመንግሥት ትምህርት ቤቶች እና የመንግሥት ቤተ-መጻሕፍት።

የመንግሥት እርዳታዎችን ማግኘት አሁንም ቢሆን DHS አንድ ሰው «የሕዝብ ሸክም» ሊሆን ይችላል ወይ በሚል በሚወስንበት ጊዜ ማየት ካለበት በርካታ ነገሮች መካከል አንዱ ክፍል ብቻ ነው። የኢሚግሬሽን ባለሥልጣናት አሁንም ቢሆን የሰውን አጠቃላይ ሁኔታ ይመለከታሉ፤ ይህም ዕድሜን፣ ገቢን፣ ጤናን፣ ትምህርትን ወይም ክህሎትን እና የቤተሰብ ሁኔታን ያካትታል።

## ጠበቃ ማማከር ያለብኝ መቼ ነው?

ይህ አዲስ መመሪያ የተወሳሰበ በመሆኑ እና የሁሉም ቤተሰብ ሁኔታ የተለያየ ስለሆነ፣ ስለ ማመልከቻዎች ወይም ጥቅማጥቅሞች ውሳኔ ከመስጠትዎ በፊት ከኢሚግሬሽን ጠበቃ ጋር መነጋገር አለብዎት።